# ፍርድን ከራስ ምርትን ከአግማስ (ቁጥር 2)

...................................ካለፈው የቀጠለ ቁጥር ሁለት

አቶ መርሻ ዮሴፍ ወያኔን ይቅርታ ጠይቀን እንግባ ሲል፣ ወያኔንም ወያኔ ማለት አይኖርብንም ሲል፣ በወያኔ ላይም ከረር ያሉ ቃላትን መጠቀማችንን እናቁም ሲል፣ ዕምነታችን ክህደት እየፀነሰ መሆኑን መጠርጠር ተስኖን ይልቁንም ያንጃው መሪ ተልዕኮውን እስኪያሟላ ገላውን ሰድዶ ተ ንቀሳቀሶ የድሮ ጓዶችን እንዲያሰባስብ ሃላፊነቱን ሰጠነው። በራሳችን ገንዘብና መዋቅር የራሳችንን መታረጃች ካራ በአንገታችን ላይ እንዲስልም ተመቻችተን ቀረብንለት።እርሱም ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ እንደ ዝሃ ጣይ እየተመላለሰ በተለይም ቶሮንቶና አትላንታ ውስጥ ብዙ ጓዶቻችንን በከለ። በድርጅቱም ውስጥ የራሱን መዋቅር ዘርግቶ ኢህአፓን አሽመደመደ። የሴራ መርፌ በወጋቸው አባለት በኩል የድርጅቱ ገንዘብና ሌላም ሌላም ነገር ለአንጃው መሪ ሁሉ በጅህ ሁሉ በደጅህ እንዲሉ ተመቻቸ።

በዚህ መልክ ተቀምጠን( ወርቁ እጀጉን) ደበበን፣ ሰለሞን ወርቅነህን፣ ተሾመን፣? የመሳሰሉ ያንጃ የመሰረት ድንጋዮችን በእንዘህላልነት አስቀመጥንለት። አቶ መርሻም በነዚህ የንጣፍ ድንጊያዎች ላይ ተረማምዶ የደም ሃውልታችንን ኢህአፓን የማፍረስ ዘመቻውን አጠናከረ። ታሪክም በኢህአፓ ውስጥ መልሶ ራሱን ደገመ። የብርሃነ መስቀልን ታሪክ።

ብርሀነ መስቀል ዕረዳ የዛሬ ሰላሳ አምስት ዓመት ገደማ የስልጣኑ መሽራረፍ ስጋት ላይ በጣለው ወቅት

- ከደርግ ጋር አብረን መስራት አለብን
- በደርግ ላይ ምንም ዓይነት ጥይት መተኮስ የለብንም
- ደርግን ፋሽሽት እያልን ፈሽሽት ያደረግነው እኛ ነን ወዘተ በማለት ይልቁንም በድርጅቱ ስም የድርድር ሃሳብ አቀረበ።ዛሬ ዶ/ር ጌታቸው ከዶ/ር ክንፈ ከወያኔው የውጭ ጉዳይ ባለስልጣን ጋር ኦታዋ ላይ እንደተደራደረው ማለት ነው።የያኔው አንጃ መሪ አቋሙንም በጋዜጣ ምስጢሩን አዋጅ አደረገ። መርሻና ጌታቸው በቴሌቪዥን ወጥተው ኣቋማቸውን ግልፅ እንዳደረጉት።ያኔ ድርጊቱ ያስደመመው የኢህአፓ ፓሊት ቢሮም ብርሀነ መስቀልን ስለ ጉዳዩ አነጋግሮት ነበር። ብርሃነ መስቀልም በጋዜጣ የወጣው ፅሁፋ ባለቤት ራሱ መሆኑንና ሃሳቡንም በነፃ የመግለፅ መብቱ መሆኑን ለማሳመን ፓሊት ቢሮውን ሞገተ። የፓሊት ቢሮውም ማንም የድርጅቱ አባል ሃሳቡን በነፃ የመግለፅ መብቱ ቢሆንም በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በድርጅቱ ስም ለመፃፍ የፓሊት ቢሮው የፅሁፋን ይዘት መመልከት እንደሚኖርበትና ይህንንም ህግ መተላለፋን ሊያስረዳው ሞከረ። ብርሃነ መስቀል ግን ህጉን ጥሶ እኔ ያልመራሁት ኢህአፓ መፍረስ አለበት ብሎ ተንቀሳቀሰ። ይብሱንም ወንጀሉን አስፋቶ ከመኤሶን ባልተናነሰ ፋሽሽታዊ ባህሪይ የድሮ ጓዶቹን ከደርግ ጋር ወግኖ አጨደ። አሳጨደ።

ብርሃነም እንደ ዛሬው አንጃ እንደ መርሻ ዮሴፍ የድርጅቱን መዋቅር ተጠቅሞ ነበር ሴራውን ማጠናከር የቻለው። የዚያኔው አንጃ ድርጅቱ ከሰንደፋ የፓሊስ ማሰልጠኛ የነጠቀውን መሳሪያ አባብሎ ባስከዳቸው አባላት በነ አራርሶ አመካኝነት ከተከዘነበት ቦታ ዘርፎ ኢህአፓ የትጥቅ ትግል ሊጀምር መሰናዶ ወደ አደረገበት ስፍራ ወደ ሰሜን ሸዋ አሸጋገረና የራሱን የአንጃ ቡድን እንቅስቃሴ ጀመረ። መርሻም ለድርጅቱ ጉባኤ ማስኬጃ በአባላት የተዋጣውን ገንዘብ በነ ደበበና (ወርቁ እጅጉ) በነ ሰለሞን ወርቅነህ አማካኝነት ለራሱ አንጃ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተከራይቶ በድርጅቱ ውስጥ ሌላ ድርጅት መስርቶ ወጣ። እዚህ ላይ ብርሃነን ለዚህ ክህደት እንዳበቁት ምክንየቶች የመርሻስ ምክኒየቶች ምንድን ናቸው? ብሎ መጠየቅ አገቦነት የሚኖረው ይመስለኛል።

እንደሚታወቀው ብርሃነ መስቀል የተማሪው እንቅስቃሴ ያፈራው አብዮታዊ ታጋይ፣ አንደበተ ርትዑ፣ቆራጥ፣ ደፋርና የተዋጣለት ፀሀፊና ጀግና ኢትዮጵያዊ ነበር። ግና ግና ሰው ያለ ዓመል አይሰራም እንዲሉ ሆነና እርሱም ሰው እንደ መሆኑ የራሱ ደካማ ጎኖች ነበሩት። ከኔ በላይ ሰው ላሳር ነው። የመሪነትንም ልጓም ከኔ ሌላ ማንም ሰው ሊጨብጣት አይችልም የሚል ራስን ከፍ አድርጎ የማየት ድክመት ነበረበት። ይህም ችግር ነበር በድርጅቱ ውስጥ የነበረውን ወሳኝ ሚና እንዲያጣ ያደረገው።

ብርሃነ ኢህአፓ እንደ ተመሰረተ የድርጅቱ ዋና ፀሃፊ፣ የሠራዊቱ ኮማንደር፣ የፓሊት ቢሮና የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ነበር። ሠራዊቱን መርቶ አሲምባ እንደ ገባ ደርግ የመሬት አዋጅ አወጀ። ይህንንም አዋጅ ያዳመጡት እነ ተስፋየ መኮንን(መኪሬድ) ድሮም የተነሳነው መሬት ላራሹ ብለን ነበርና የመሬት ጥያቄ ከተመለሰ ምን የሚያታግለን ነገር አለ ብለው ከሠራዊቱ ከድተው እጃቸውን ለድርግ ሰጡ። ብርሃነም የነዚህን ከሃዲዎች ስራ ሰራዊቱን ሰብስቦ በመወንጀል የሞት ፍርድ አስበየነባቸው። ፍርዱንም ባስቸኳይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው በማሳሰብ ለማዕከላዊ ኮሚቴው የፍርዱን ውሳኔ አስተላለፈ።ማኮው ግን ድሮውንም ሁላችንም ኢህአፓን ስንቀላቀል በራስ ፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተ ፍላጎት ስለነበር ማንም ታጋይ ሳይፈልግ ድርጅቱን ጥሎ የመውጣት መብቱ ነውና ለምን ወጡ ብሎ በሞት ብያኔ መቅጣት ፍትሃዊ አይሆንም ብሎ ቢቻል አብሮ አለያም በጋራ መስራት እንደሚፈልግ በማነጋገር ነገሩን በለሆሳስ ይዞት ቆየ።ሰኛና ሰኔ ሲገጣጠሙ እንዲሉ የመስላል በዚሁ ወቅት በክረምቱ ወራት

ድርጅቱ ጉባኤ ጠርቶ ስለ ነበር ብርሃነም የፍርዱን ውጤት በዚሁ ስብሰባ መረዳት በቃ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉም ከዋና ፀሃፍነቱ፣ ከሠራዊትአዛዥነቱና ከፖሊት ቢሮ አባልነቱ ወረደ። በዚያ ጉባኤ ስልጣኖቹ በሙሉ ተነጠቁ።ይህም ሁኔታ ብርሀነ መስቀልን ለኔ ያልሆነ ኢህአፓ ይበጣጠስ ወደሚል ስህተት ዘፈቀውና አንጃ ሆኖ ኢህአፓን ለመበተን ቆርጦ ተነሳ።የመርሻ ዮሴፍ አንጃነትም መንስኤው ከዚህ የተለየ አይደለም ።

መርሻም በራሱ ጫማ የሚለካ እንደ ብርሃነ መስቀል፣ ጀግንነትና፣ ቁርጠኝነት፣ በውስጡም የሚነድ ያገርና የህዝብ ፍቅር ነበረው።ግን ሲያልቅ አያምር እንዲሉ ሆነና ባለቀ ዕድሜ ታሪኩን ትቢያ ላይ የወደቀ ስጋ አድርጎ ብርሃነ መስቀል በተጓዘበት መንገድ ተጓዘ። ወደ ማእከላዊ ኮሚቴ የመጣው መርሻ ከብተና በሁዋላ በተካሄደው ሁለተኛው ገባኤ ነበር።ቋራ ላይ። ከዚያ በፊት ተለዋጭ የማኮ አባል ነበር።

ሙሉ የማእከላዊ ኮሚቴ አባልነቱን እንዳገኘም የተበተነውን የድሮ ታጋይ ሀይል የማሰባሰብ ሃላፊነት ከፋሲካ በለጠ ጋር ተረክቦ ወደ ሰሜን አሜሪካ አቀና። የማደራጀቱን ስራ ገና ሀ ሲጀምር ኢህአፓ በሶስቱ ጠላቶቹ በሱዳን፣ በሻቢያና በወያኔ ጣምራ ሃይል ቋራላይ ተጨፈጨፈ። መሪዎቹም እነ ፀጋየ ደብተራው፣ ይስሃቅ ደብረፂዎን፣ስጦታው ሁሴንና ሌሎቹም በጠላት እጅ ወደቁ። የመሪነቱም ሃላፊነት በመርሻና በፈሲካ ትከሻ ላይ ወደቀ። በዚህም መሃል ኢድሀቅ ተመሰርቶ መርሻ ዮሴፍ ሊቀ መንበር ሆኖ ተመረጠ።የመርሻ ስልጣንም እንደ ብርሃነ መስቀል ስልጣን መከማ ቸት ጀመረ። ኢድሃቅን ወክሎ ወደ አዲሰ አበባ ለመሄድ እስከ ተነሳበት ጊዜ ድረስ በሁለቱም ሀይሎች ከፍተኛውን ስልጣን ጨብጦ የነበረው መርሻ ነበር። ካይሮ ላይ እንዳለ ነበር እነዚህ ስልጣኖቹ በሙሉ እንደ ብርሃነ መስቀል ስልጣኖች በድንገት ከዕጁ ያፈተለኩት።።። የመርሻ ስምም ከ 6ዚያን ጊዜ ጀምሮ በየ ጋዜጣውና በየሬዲወው መነሳቱ ቀመ። በምትኩም የፋሲካ ስም እየጎላ ሄደ። በተለይም በህብረቱ ምስረታ ፋሲካ በከፍተኛ ድምፅ ለከፍተኛ ስልጣን ሲመረጥ መርሻ ግን በአምስት ድምፅ መሸነፉ ነበር ለተስፋ መቁረጡ እንዱ ምክኒያት።

አብራሃም በየነ ይቀጥላል............